## *ቅዱስ ፍራንችስኮስ ከምድራዊ ህይወቱ ወደ ሰማያዊ ቤቱ የተሸጋገረበት የዋዜማ ስነ- ስርዓት*

*(ስነ - ስርዓቱ የሚጀምረው አመቺና በጥሩ ሁኔታ ባጌጠ ቦታ መሆን አለበት። ተሳታፊዎቹ በቅዱስ ፍራንችስኮስ ሐውልት ( ሥዕል) ዙርያ ከተሰብሰቡ ቦኃላ ሻማዎችን ያብሩ፡፡)*

***መሪ፡-*** ወንድሞችና እህቶች ሆይ አባታችን ቅዱስ ፍራንችስኮስ ከምድራዊ ህይወቱ ወደ ሰማያዊ ቤቱ የተሸጋገረበት ዕለት ዋዜማ ለማክበር እዚህ ተሰብሰበናል። ይህ ሥርዓት ከጥንት ጀምሮ በባህልችን ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣና የአባታች የቅዱስ ፍራንችስኮስ የመጨረሻ ጉዞ የምናስብበት ሥርዓት ነው ፡፡ ስለዚህ የፃድቁን አባታችን የዕረፍቱ ቀን እያሰበን በክብር ወደ መንግስተ ሰማይ በመግባቱ እንደሰታለን። እኛም እንደ ቅዱሱ አባታቻን በእግዚኣብሔር ምህረት እየታመንን እህት ሞትን በፀጋ ለመቀበል ከአሁኑኑ በትንሳኤው ተስፋ እናድርግ ፡፡

***አለቃ ፡-*** የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ ፤ የእግዚአብሔር ፍቅርና የመንፈስ ቅዱስ አንድነት ከሁላችሁ ጋር ይሁን ፡፡

***ሁሉም ፡-*** ከመንፈስም ጋር

***አለቃ ፡-*** (***እንፀልይ)*** እግዚአብሔር አምላክችን ሆይ፤ ለአሲዚው ድሃ ለአባታችን ቅዱስ ፍራንችስኮስ የፍፅምና ሙላት ሽልማት ሰጠኸው፡፡ በዚህ በምናከብረው የሞቱ ቀን ዋዜማ እኛም በሙላት የርሱን ፈለግ በመከተል የማያልቀውን ደስታህ ተካፋዮች እንድንሆን ካንተና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አብሮ በሚኖረውና በሚነግሰው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እንለምናለን።

***መሪ ፡-*** አንድ የቆዬ ጥሩ አባባል አለ፤ "የአንድ ሰው የመጨረሻ መሻት በኑዛዜው ይገለጻል።" ይህ አባባል በቅ. አባታችን በማያዳግም ሁኔታ ተፈጻምነት አገኝቱዋል። እርሱ እንደ ማለዳ ጸሐይ የሚያበራ ሆኖ በተረፈረፈ ጸጋዎች አሸበረቀ። በኑዛዜውም እንደተናገረው ይህንን የመለወጥ ጉዞ የጀመረው እግዚአብሐር እራሱ ስለመራው ነው። እስቲ የእርሱን የኑዛዜ ቃል እንስማ፡-

***አንባቢ፡-*** ከቃለ - ኑዛዜ 1፡6 እና 10.

***መሪ፡-*** ከዚያም የሞቱ ዕለት መቃረቡን ባወቀ ጊዜ ከወንድሞቹ መካከል መንፈሳዊ ልጆቹ ከነበሩት ሁለቱን ማለትም ወንድም ሊዮንና አንጀሎን አስጠርቶ የሞቱ ቀን መቃረቡና ይልቁንም ስለሚጠብቀው አዲስ ህይወት በከፍተኛ ድምፅ ፤ በልባዊ ደስታ ለእግዚኣብሔር የምስጋና የውዳሴን መዝሙሮች እንዲዘምሩ አዘዛቸው ( 1ኛ ቸላኖ 109 )።

***ሁሉም ፡-*** ለፍጥረታት ሁሉ የደረሰው ማህሌት ሁሉም በጋራ ይዘምሩ፡-

### እንደ ፍራንችስኮስ

እንደፍራንችስኮስ ጌታን እናመስግነው
በፍጥረቱ ሁሉ ዘወትር እንወድሰው
ሁሉን ቻይ ነውና ጌታን እናከብረው
ስላደረገልን ተመስገን እንበለው

ጌታ ሆይ ተመስገን በወንድም ፀሀይ
በጨረሩ ድምቀት ያበራልን ፀሀይ
አምላኬ ተመስገን በወንድም ነፋስ
በአየሩ ሁኔታ ስምህ ይቀደስ

ተመስገን ጌታ ሆይ በወንድም እሳት
ደግና አስደሳች ሩህሩህ ፍጥረት
እንዲሁም ተመስግን በእህታችን ሞት
የዘለዓለም ህይወት የምትገኝባት

ምስጋና ይድረስህ በእህታችን መሬት
ትመግበናለች ዕለት በዕለት

ተመስገን ጌታ ሆይ በእህታችን ውሃ
ጠቃሚና ትሁት የሰው ልጅ ፍስሃ

ጌታ ሆይ ምስጋናህ ለዘለዓለም ነው
ዓፈር አድቦልቡለህ ስለፈጠርከው ሰው
በአምሳያህ አድርገህ ስለሰራኸው
በስው ዘንድምስጋና ሁሌ ላንተ ነው

***መሪ*** ፡- ቅዱስ ፍራንችስኮስ ሁሉም ወንድሞች እንዲሰበሰቡ ካደረገ ቦኃላ የሞቱን መቃረብ በዓይነ-ህሊናው እየቃኘው ሁሉንም እያረጋጋቸውና እያጽናናቸው በሰከኑ ቃላቶች ከሁሉም በላይ እግዚአብሔርን በተቃጠለ ፍቅር መውደድ እንዳለባቸው መከራቸው፡፡ እጅግ ልዕልት ድህነትን ከሁሉ በላይ የህወታቸው ልዩ ድርሻ እንዲያደርጓትና በወንጌላዊ ህይወት እንዲታጠቁ ለረጅም ጊዜ አስተማራቸው ፡፡ ከዚያም ከዋና አለቃው ጀምሮ በእያንዳንዱ ወንድም ራስ ላይ ቀኝ እጁን ዘርግቶ እዚያ የተገኙትንም በተለያየ ክፍለ አለም ያሉትንም ፤ ወደፊትም የሚመጡትን ሁሉ ባረካቸው ( 2ኛ ቸላኖ 216 )፡፡

***አለቃ፡- በቅዱስ ፍራንቸስኮስ ቡራኬ ሁሉንም ይባርክ፤***

> እግዚአብሔር ይባርክህና ይጠብቅህ፤
> የፊቱን ብርሃን ይግለጥልህ ይራራልህም፤
> በምህረት አይኑ ይመልከትህ፤
> ደስታውንና ሰላሙን ይስጥህ ፡፡

***መሪ*** ፡- ይሁን እንጂ ከወንድሞች መካከል ቅዱስ ፍራንችስኮስ በጣም ይወድ የነበረው አንድ ወንድም በጥልቅ ጭንቀትና ሃዘን በተቀላቀለበት ስሜት ለቅዱሱ እንዲህ አለ፤

***ወንድም ( እህት )*** ፡- ደግ አባት ሆይ ልጆችህ የዓይኖቻቸውን ብርሃን በማጣት አባት አልባ፤ ምስኪን ተነከራታቾች ሊሆኑ ነው፡፡ አንተም ወደ ዘለዓለማዊ ቤትህ አሁን እየሄድክ ነው፤ ስለዚህ እኛን አባት አልባ ልጆችህን አስታውሰን ፡፡ እዚህ የተገኙትንም ያልተገኙትም ሁሉ ደስታን ስጣቸው ፤ ከበደላቸውና ከስህተቶቻቸው ይቅር በላቸው፤ በቅዱሱ ቡራኬህም ባርካቸው ፡፡

***መሪ*** ፡- ቅዱስ ፍራንችስኮስም እንዲህ አለው፤

***አለቃ*** ፡- የእኔ ልጅ! እነሆ እግዚአብሔር ወደርሱ ጠርቶኛል ፡፡ በሚቻለኝም እዚህ የተገኙትንም ያልተገኙትንም ወንድሞቼን ሁሉ እባርካቸዋለሁ፤ ከስህተታቸውና ከበደላቸውም ይቅር እላቸዋለሁ፡፡ ስለ እኔ ይህንን ለእነርሱ እንድታውጅና እንድትባርካቸውም እፈልጋለሁ ፡፡

***መሪ*** **፡-** በመጨረሻም መፅሐፍ ቅዱስ እንዲያመጡለት ጠየቀ፤ «ለትንሳኤ በዓል ስድስት ቀናት ሲቀሩት.........» ከሚለው ጀምሮ ከዮሐንስ ወንጌል እንዲያነቡለት አዘዘ፡፡

**አንባቢ ፡-** **(ከዮሐንስ ወንጌል ም. 13፡ 1 – 20)**

- **( ስብከት ወይም የአስተንትኖ ጊዜ )**

***መሪ*** **፡-** ወንድሞች ሁሉ በመሪር ሀዘን መፅፅናናት ተስኖዓቸው ሳሉ ፤ ቅዱስ አባት ዳቦ እንዲያቀርቡለት አዘዛቸው ፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጨረሻ እራቱን ከደቀ - መዛሙርቱ ጋር መብላቱን በማስታወስ ባርኮ ፤ ቆርሶም ለእያንዳንዳቸው አደላቸው ፡፡

***አለቃ*** **፡-** *( ዳቦውን ይባርካል )* **ጸሎት፡-** የሰማይና የምድር ንጉሥ ቅዱስ ፤ ሃያልና ትክክል የሆንክ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ሆይ፤ ላንተ ብቻ ምስጋናን እናቀርባለን ፡፡ በፈቃድህ መንፈሳዊና ጊዜያዊ ነገሮችን ፈጠርህ ፤ በልጅህና በመንፈስ ቅዱስ ሃይል በመንግስተ - ሰማይ አንተን የምንመስልበትን ቦታ አዘጋጀህልን ፡፡ ስለዚህ እህት መሬት የሰጠችንንና በወንድሞች እጅ የተዘጋጀውን ይህንን ዳቦ በጌታችን በኢየሱስ በክርስቶስ ህይወት ውስጥ ተሳታፊዎች እንዲያደርገን ፤ አሁንም ለዘለዓለምም ካንተ ጋርና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በሚኖረውና በሚነግሰው በምትወደው ልጅህ እንለምንሃለን ፡፡

- **( የዳቦው ዕደላ ስነ - *ሥርዓት*፡፡ በዚህን ጊዜ ዶቦ በጸጥታ ይቆረሳል /ከ5 እስከ 6 ደቂቃ ጸጥታ ጊዜ ይጠበቅ)**

***መሪ*** **፡-** ከዚህ ቦኃላ ቅዱሱ ልብሶቹን አውልቆ በመሬት ላይ አንጥፎ ተኛ፡፡ እንደልማዱም ፊቱን ወደ ላይ ቀና አድርጎ በሁለመናውም ሰማያዊ ክብሩን እየቃኘ ፤ ይታዩ የነበሩትን ቅዱሳት ቅንዋቶቹን ሸፍኖ ለወንድሞቹ ሁሉ እንዲህ አላቸው ፡-

***አለቃ*** **፡-** እኔ ማድረግ ያለብኝ አድርጌአለሁ፤ ክርስቶስ እናንተንም ማድረግ ያለባችሁን ይግለጥላችሁ፡፡

***መሪ*** **፡-** ከጥቂት ቆይታ በኃላ አለቃው በጥድፊያ ከተቀመጠበት ተነስቶ ቅዱስ ፍራንችስኮስ ምንም ልብስ በላዩ ላይ እንዳይኖር በመፈለጉ ሌላ አንድ ቀምስ ይዞ መጥተው በተአዚዞ ቃል እንዲህ አለው ፤

**ወንድም ( እህት )፡-** ይህንን ቀምስ ለእንተ እንዳበደርኩ ልብ በል፡፡ ከእኔ የተበደርከው ስለሆነ አውልቀ ለመጣል ሆነ ለሌላ ለመስጠት መብት እንደለሌ እወቅ አለው፡፡

***መሪ*** **፡-** በዚያን ጊዜ ቅዱስ ፍራንችስኮስ እስከ መጨረሻ ድረስ ለልዕልት ድህነት በመከተሉዋ በመንፈሱ ተደሰቶ አለቃ ያመጣለትን ቀምስ ተቀበለ፡፡ ከዚያም በደከመ ድምፅ መዝሙር 142ን ደገመ፤ በዙሪያው ያሉትም ሁሉ አብረውት መድገም ጀመሩ ፡፡

- **(ሁሉም መዝሙሩን ይድገም)**

ድምጼን ከፍ አድርጌ ወደ እግዚአብሔር እጮኻለሁ፤
ምህረት እንዲያደርግልኝ እለምነዋለው፡፡
አቤቱታዬን ሁሉ አቀርባለሁ፤
ችግሬንም ሁሉ እነግረዋለሁ፡፡
ተሰፋ ለመቁረጥ ጥቂት በቀረኝ ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚገባኝ ያውቃል፤

ጠላቶቼ በምሄድበት መንገድ ላይ ወጥመድ ዘረጉብኝ።
በዙሪያዬ ስመለከት መሸሸጊያ የሚሆን አጣውት፤
አንድም እንኳን ያሚረዳኝ ሰው አልነበረም፤

የሚጠብቀኝና የሚጠነቀቅልኝም አልነበረም።
እግዚአብሔር ሆይ! እንድትረዳኝ ወደ አንተ እጮኻለሁ፤
እግዚአብሔር ሆይ! ጠባቂዬ አንተ ነህ፤
በሕያዋን ምድር ዕድል ፈንታዬ አንተ ነህ።

በጣም ተስፋ የቆረጥሁ ስለሆነ እንድትረዳኝ ወደ አንተ ስጮኽ ስማኝ፤
እጅግ በርትተውብኛልና ከጠላቶቼ አድነኝ።
አመሰግንህ ዘንድ ከእስራቴ አውጣኝ፤
ለእኔ ያደረግኸውን ያንተን የቸርነት ሥራ በሚያዩበት ግዜ፤ ሕዝብህ በዙርያዬ ይሰበሰባሉ።
**ለአብና ለወልድ....................**

***መሪ*** **፦** ቅዱስ የእግዚአብሔር ሰው የህይወቱ ፀሃፊዎች እንደዘገቡት፤ እሱ እራሱ ቀድሞ እንደተነበየው የቅድስና ጉዞ በጀመረበት በሃያኛው ዓመት፤ እ. አ. አ. በጥቅምት 3 ቀን 1226 ዓ/ም ከስጋዊ ህወት እስራት ተላቅቆ ወደ ሰማያዊ ህይወት ተሸጋገረ። በምድር ላይ እያለ በህይወቱ የተከተከተለውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ፊትለፊት ለማየት ወደሰማያዊ ቤቱ በደስታ ተሸጋገረ (2ቸላኖ 220)።

- ***ከዚህ ቀጥሎ ወንድም ኤልያስ የቅዱስ ፍራንችስኮስ ሞት በማስመለከት ያጻፈው ደብዳቤ ይነበባል***
- ***ደብዳቤው ከተነበበ ቦኃላ መብራቶቹ ጠፍቶ ሁሉም በፀጥታ በቅዱስ ፍራንችስኮስ ሞት ያስተነትናሉ***

***መሪ*** **፦** ቅዱስ ፍራንችስኮስ ነፍሱ ከስጋው በተለየችበት ቅፅበት ወንድሞች በደስታ ነፀብራቅ ጠቦት የሚመስል ምስል አዩ ፤ ይህም ጠቦት ከተቸነከረበት መስቀል የወረደ ይመስል ነበር። እግሮቹና እጆቹ በጦር እንደተወጉ የመስሉ ነበር፡፡ እነርሱም በፍጥነት ቁስሎቹን ለመሳም ተጠጉ፡፡ ይህም ክስተት አለምን ከአባቱ ጋር ያስታረቀውን የክርስቶስን ስቃይና ሞት በአይነ ሕሊናቸው አስቃኛቸው፡፡

**ሁሉም፦** ቅዱስ አባት፤ የዓለም ብርሃን፤ የፍራንችስካውያን አርዓያ፤ የመልካም ነገር ሁሉ መስተዋት፤ የስነ-ምግባር መስፈርት የሆንክ አባት ሆይ እኛም ከዚህ ዓለም መጻተኝነት ወደመንግስትህ በሰላም እንድንሄድ አድርገን።

**አሊቃ (እንጻልይ)፤** ሱራፌላዊ አባታችን ቅዱስ ፍርንችስኮስ ሆይ! ይህችን ዓለም ትተህ ወደ ሰማያዊ ቤትህ በተጓዝክባት በዚያች መጨሻ ቀን በሁሉ እድሜ ክልል ያሉትን ልጆችህን እንደባረክህ ሁሉ፤ እኛንም በተሰቀለው ክርስቶስ ስምና በሃይሉም የሞትህን ዋዜማ ምሽት ለመዘከር የተሰበሰበነውን ተመልከት። በቀሪው ጊዜያችንም የአንተ ተልእኮ የምንቀጥልበት ጸጋ እንድትሰጠንና ለተተኪ ወንድማቻችንና እህቶቻችን የአንተን ብርሃናዊ ህይወት መመስከር እንድችል ከእርሱና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አብሮ በሚኖረውና በሚነግስሁ በልጅህ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንለምንያልን።

**ህዝብ፤** አሜን።

- **በመጨረሻም የመዝጊያ መዝሙር እየተዘመረ ሁሉም ሻማዎቻቸውን አብርተው በፍራንችስኮስ ስዕል አጠገብ ባማኖር የስርዓቱ ፍጻሜ ይሆናል።**

## አምላኬ

እንደ ፍራንችስኮስ ልቤን ለውጥልኝ
የሰላም መሣርያ እንድሆን ዘድርገኝ
በሕይወቴ ሁሉ አንተን እንዳስከብር
እንድሆንልህም የአንተ ምስክር

## አዝ፡ አምላኬ /3/ ሁለንተናዬ

አንተን ብቻ ወዶ አለም እንደተወው
ገንዘቤም አንተው ነህ ትዳሬም አንተው
ብሎሁሉም ትቶ ወደአንተ እንደመጣው
እንደ ፍራንቸስኮስ ሕይወቴን አድሰው

እመቤት ድህነትን እንደ እንዳደረገው
ሀብቱን ንብረቱንአንተን እንዳደረገው
እንደ ፍራንቺስኮስ እኔም ድሃ ሆኜ
አንተን ላገልግልህ መሳሪያህም ሆኜ

የዓለምን ደስታ ሀብትን ሁሉ ትቼ
አንተን ላፍቅርህ እራሴን ሰጥቼ
በፍቅርህ ልንደድ ልቃጠልልህ
እንደ ፍራንቺስኮስ እንባዬ ይፍሰስልህ

በወንድም ፀሀይ ጨረቃ እያልኩኝ
ፍጥረትን ሁሉ ወዳጄን አረኩኝ
በህይወቴ ሁሉ አንተን ብቻ ላስብ
እንደ ፈፍራንችስኮስ ምስጋናዬን ላቅርብ

--------------------- *ተፈጸመ* --------------------